

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ስድስተኛ ክፍል











በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ
ስድስተኛ ክፍል



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ 2015 ዓ.ም

ያግኙን

Email
office@eotc-gssu.org
YouTube
https://www.youtube.com/channel/UC83LE1vp0FBsV2TEfcpSmUg
Facebook
http://facebook.com/EOTC.GSSU
Telegram
https://t.me/EOTCNSSU
Website
https://eotc-gssu.org/a/
Twitter
https://twitter.com/tibeb_felege

Copyright ©
2015



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት



ብፁዕ አቡነ አብርሃም የጠቅላይ ቤተክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የባህርዳር ሁገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ



ብፁዕ አቡነ ቀለሜንጦስ በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምርያ የበላይ ሊቀጳጳስና የሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ

የቤተክርስቲያን ዘይቤአዊ ፍቺ..... ፱

፩.፩ ማኅበረ ምእመናን/ የክርስቲያኖች አንድነት..... ፱

፩.፪ የክርስቲያኖች ሰውነት..... ፱

፩.፫ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን..... ፲

ምዕራፍ ሁለት

የቤተክርስትያን ባሕርይ

፪.፩ አንዲት ናት..... ፲፬

፪.፪ ቅድስት ናት..... ፲፭

፪.፫ ሐዋርያዊት ናት..... ፲፯

፪.፬ የሁሉና በሁሉ ያለች ናት..... ፲፯

፪.፭ በሰማይም በምድርም ያለች ናት..... ፲፰

ምዕራፍ ሦስት

የቤተክርስቲያን ስያሜ በሊቃውንት

፫.፩ ቤተክርስቲያን ዘእግዚአብሔር..... ፳፪

፫.፪ ቤተክርስቲያን..... ፳፪

፫.፫ ቤተክርስቲያን ዘክርስቶስ..... ፳፫

፫.፬ ማኅደረ እግዚእ..... ፳፬

፫.፭ የጸጋው ግምጃ ቤት የምሕረቱ ማኅደር..... ፳፬

፫.፮ ቤተክርስቲያን ሰርክ ሐዲስ..... ፳፭

ምዕራፍ ዐራት

የቤተክርስቲያን እድሜ

፬.፩ በዓለመ መላእክት..... ፳፰

፬.፪ የደጋግ አበው አንድነት,..... ፳፱

፬.፫ የክርስትያኖች አንድነት..... ፴

ምዕራፍ አምስት

ቤተክርስቲያንና ምሳሌዎቿ

፭.፩ የቤተክርስቲያን ምሳሌዎች በብሉይ ኪዳን..... ፴፫

፭.፩.፩ ጠፈር..... ፴፬

፭.፩.፪ ገነት..... ፴፬

፭.፩.፫ የአብርሃም ድንኳን..... ፴፭

፭.፩.፬ ቤቴል..... ፴፭

፭.፩.፭ ደብተራ ኦሪት..... ፴፭

፭.፩.፮ ደብረ ሲና..... ፴፮

፭.፩.፯ ምኩራብ..... ፴፮

፭.፩.፰ የኖኅ መርከብ..... ፴፯

፭.፩.፱ የያዕቆብ ሐውልት..... ፴፰

፭.፩.፲ ደብረ ታቦር..... ፴

፭.፪ የቤተክርስቲያን ምሳሌዎች በሐዲስ ኪዳን..... ፵፩

፭.፪.፩ የአሳ ማጥመጃ መረብ..... ፵፩

፭.፪.፪ የሰርግ ቤት..... ፵፩

፭.፪.፫ የአልዓዛር ቤት ምሥጢረ ቁርባን የተደረገባት..... ፵፪

፭.፪.፬ የማርቆስ እናትየማርያም ቤት..... ፵፪

፭.፪.፭ ሕንፀተ ቤተክርስቲያን..... ፵፫

ዋቢ መጻሕፍት

መግቢያ

ሀ) የታሪክ ምንነት

ታሪክ ያለፈ የተጻፈ ወሬ ወይም ዜና መሆኑን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ሲገልጹ፤ ደስታ ተክለወልድ የተባሉ ምሁር ደግሞ በቃል እና በጽሑፍ ሲያያዝ የመጣ ዜና መዋዕል ስለመሆኑ ተርጉመዋል የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ አማርኛ መዝገበ ቃላት "ታሪክ የአንድ ነገር ሁኔታ ዕድገት እና ሂደቱን የሚያሳይ ዝርዝር ትንተና በተጨማሪም በጊዜ ቅደም ተከተል የሚሄድ ስላለፈው የሕዝብ፣ የመንግሥት ድርጊት እና ሁኔታ የሚያጠና የጎበረተሰብ ሳይንስ ነው ይላል።

"ሂስትሪ" የሚለው ቃል "ሂስቶሪያ ከሚለው የጽርኡ ቃል የተገኘ ሲሆን "ምርመራ፣ በምርምር የሚገኝ ያለፈ ሁኔታን የሚያጠና ዕውቀት" ስለመሆኑ የዘርፉ አጥኚዎች ይናገራሉ። ቅ.ል.ክ 492 ዓመት ገደማ የነበረው ሄሮዶቶስ ታሪክን ሲተረጉም "የተተረከን ነገር ተመራምሮ የሚያረጋግጥ ዕውቀት ነው" ብሏል።

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ ላይ የተመሠረተ ነው። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ስንል ክርስትና እንዴት እንደተመሠረተ፣ እንዴት እንደተላለፈ፣ ወርቃማ እና የመከራ ጊዜያትን እያተተ የሚዘረዝር የዕውቀት ዘርፍ ነው። በመሆኑም በዚህ ትምህርት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክን ለመጠቆም ይሞክራል።

ለ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመማር አስፈላጊነት

ዛሬ የትናንት ፍሬ፣ የነገ ዘር ነው እደሚባለው ዛሬ እና ነገን ውጤታማ ለማድረግ ከትናንት መማር ያስፈልጋል ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

መማር

፭. ዛሬን ለመረዳት ያስችላል- ማለትም ከየት ጀመርን፣ እንዴት አሳለፍን፣ እስከ አሁን እንዴት ደረስን? የሚለውን ጥያቄ መልስ ይሰጠናል፤

፮. ታሪክን ማወቅ ለበጎ ሥራ የሚያተጋ ኃይል ነው፡- መልካም ከሠሩት ተምረን በሃይማኖት በምግባር እንድንተጋ ምክንያት ይሆነናል “ተዘከሩ መኳንንቲክሙ...” ዕብ. ፲፫፥፯ እንዲል

፫. ማንነትን ለማወቅ እና ታሪክን ለማስቀጠል- የቤተ ክርስቲያን ታሪክ መማር ማንነትን ለማወቅ አስፈላጊ ነው። “የቀደመውን ትውልድ ጠይቅ...” ኢዮ.፰፥፰ እንዲል በአጠቃላይ በዕውቀት ላይ የተመረኮዘ ኑሮ እና አገልግሎት እንዲኖረን እንደዚሁም ለትውልድ ታሪክን ለማስተላለፍ ታሪክ መማር፣ ማንበብ ጠቃሚ ነው። “አስቀድሞ የተጻፈ ሁሉ ለትምህርታችን ተጻፈ” ሮሜ.፲፭፥፬

ሐ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምንጮች (መገኛዎች)

ታሪክ ሳይሳዊ (ምርምራዊ) ሂደት ስለመሆኑ ከላይ ገልጸናል፡ ስለሆነም ለሚነገረው ሁሉ እውነታነትን ለማረጋገጥ መገኛው (ምንጩ) ወሳኝ ነው። ያለበለዚያ ተረት እንጂ ታሪክ ለማለት አያስችልም ምሁራን ስለታሪክ ምንጭ ሲያትቱ በሁለት ይከፍሉታል።

፩. ጽሑፋዊ ያልሆኑ ምንጮች (Primary Source)

- በጽሑፍ ያልሆኑ በተለያዩ ሁኔታዎች በምርምር የሚረጋገጡ ምንጮች አሉ ለአብነት
- ጥንታዊ የመቃብር ሥፍራዎች
- አብያተ ክርስቲያናት ወይም የቤተ መቅደስ ፍርስራሾች ፤

ለምሳሌ፡- (በኢትዮጵያ ሥርዓተ አሪት ስለመኖሩ “መሥዋተ አሪት” መገኘቱ ማስረጃ ነው።

- ጥንታዊ የአብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ
- ሥዕላት፣ ሥርዓተ አምልኮ...
- ሳንቲሞች፣ ንዋያተ ቅድሳት፣ ቅሪተ አካል.....

፪. የጽሑፋዊ ምንጮች (Secondary Sources)

በተለያዩ ዘመናት በጽሑፍ የተገኙ ምንጮችን ያመለክታል

- ብሉይ ኪዳን እና ሐዲስ ኪዳን
- የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጻፏቸው መጻሕፍት
- ሲኖዶሳት፣ የጉባኤ ውሳዎች
- ነገሥታት ስለ ቤተ ክርስትያን የደነገጓቸው ሕጎች
- ነገሥታት በየዘመናቸው ሕዝብን ለማስተዳደር ያወጧቸው ሕጎች
- ገድላት እና ድርሳናት
- ዜና መዋዕሎች
- ምስክር የሆኑ ታሪኩን የጻፉ የባለሙያዎች ሥራዎች
- በመቃብር፣ በድንጋይ፣ በሥዕላት፣ በዋሻ ተጽፈው የተገኙ የመሳሰሉት...

ከጽሑፋዊ ምንጮች ይጠቀሳሉ።

ምዕራፍ አንድ

የቤተክርስቲያን ዘይቤአዊ ፍቺ



ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ

- ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል ፍቺ ወይም ትርጉም መናገር ይችላሉ
- ሦስቱን የቤተ ክርስቲያን ዘይቤያዊ ፍቺዎች በዝርዝር ይገልጻሉ።



የመክፈቻ ጥያቄዎች

- ፩ ቤተክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

ቁልፍ ቃላት

. ቤት ፡- መኖሪያ ፣ማደሪያ
/ ክርስቲያን ፡- በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት የሚያምንና የተጠመቀ
. ማኅበር ፡- አንድነት፣ ጎብረት
. ምእመናን ፡- አማኝ፣ ተከታይ
. ዘይቤ፡- አባባል፣ አገላለጽ፣አነጋገር

፩.የቤተክርስቲያን ዘይቤያዊ ፍቺ

ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ‹‹ቤት›› እና ‹‹ክርስቲያን›› ከሚሉ ሁለት የግእዝ ቃላት ጥምረት የተፈጠረ ሲሆን የክርስቲያን ቤት፣ማደሪያ፣ መሰብሰቢያ፣ የጸሎት ሥፍራ ማለት ነው።።
ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ዘይቤያዊ ፍቺዎች አሉት።። እነዚህም እንደሚከተለው እንመለከታለን።።

፩.፩.ማኅበረ ምእመናን/የክርስቲያኖች አንድነት

ቤተ ክርስቲያን ማለት የክርስቲያኖች ማኅበር፣ የክርስቲያኖች ጎብረት ወይም የምእመናን አንድነት ማለታችን ነው።።ምእመናን የሚባሉት በገታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክነት አምነው የተጠመቁትን ነው።። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሲባል የእምነቱን ተከታዮች ምእመናን ሁሉ አንድነት የሚመለከት ነው።። ይህም ጎብረት ቅዱሳንን፣መላእክትንና በአፀደ ነፍስ ያሉትን ሁሉ ያካትታል።።

፩.፪ የክርስቲያኖች ሰውነት

ክርስቲያኖች የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በመሆናቸው የእግዚአብሔር ማደሪያዎች ናቸው።። ቅዱስ ጳውሎስም በ፩ኛቆሮ ፫፥፲፮-፲፯ ላይ ‹‹የእግዚብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?›› በማለት ይናገራል።። ይህም የክርስቲያኖች ሰውነት የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆኑን ያረጋግጣል።።በዚህ ምክንያት የእያንዳንዱ ክርስቲያን ሰውነት ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ሊጠራ ይችላል።።

፩ኛ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን

በዚህ አገላለጽ ቤተ ክርስቲያን ስንል ተሰብስበን የምንጸልይበትን፣ የምናስቀድስበት፣ የምንቆርብበት፣ ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳን ምስጋና የምናቀርብበት፣ የወንጌልን ቃል የምንማርበት ሥፍራና በዚያ ሥፍራ የሚገኘውን ሕንጻ ማለታችን ነው።

አንድ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ይባል ዘንድ በኤጲስቆጶስ ፈቃድ የታነጸ፣ የተባረከ፣ የእግዚአብሔር ታቦት በውስጡ የሚቀመጥበት መሆን ይገባዋል። ይህ ካልሆነ ማንኛውም ቤተ ጸሎት ስለተጸለየበት፣ ወንጌል ስለተሰበከበት ብቻ ቤተ ክርስቲያን ሊባል እንደማይችል መረዳት ያስፈልጋል።

የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ‹‹ቤት›› እና ‹‹ክርስቲያን›› ከሚሉ ሁለት የግእዝ ቃላት የተፈጠረ ነው።
- ቤተ ክርስቲያንማለት የክርስቲያኖች ቤት፣ የክርስቲያኖች መሰባሰቢያ፣ የጸሎት ሥፍራ ማለት ነው።
- ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ዘይቤያዊ ፍቺዎች አሉት
- ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ማኅበረ ምእመናን ሊያመለክት ይችላል
- ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የእያንዳንዱን ክርስቲያን ሰውነት ሊያመለክት ይችላል።
- ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል የቤተ ክርስቲያን ሕንጻና ሕንጻው የሚገኝበትን ስፍራ ሊያመለክት ይችላል።
- አንድ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ሊባል የሚችለው ሕንጻው በኤጲስቆጶስ ፈቃድ የተሠራ፣ የተባረከ፣ በውስጡ የእግዚአብሔር ታቦት የሚገኝበት፣ ምእመናን ዘወትር የሚጸልዩበት፣ ቅዳሴ የሚቀደስበት፣ ቁርባን የሚቆረብበት ሲሆን ብቻ ነው፡

የማጠቃለያ መልመጃ

ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን ምላሽ ጻፉ፡፡

፩ ቤተ ክርስቲያን የሚለውን ቃል የፈጠሩት ሁለት ቃላት.....
እና..... የሚሉት ቃላት ተጣምረው ነው፡፡

፪. ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ምን ያህል ዘይቤያዊ ፍቺዎች አሉት?

ምዕራፍ ሁለት

የቤተክርስቲያን ባሕርይ

ዓላማ
ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ

- የቅድስት ቤተክርስቲያንን ባሕርያት ይለያሉ
- የቤተክርስቲያንን ባሕርያት አንድ በአንድ ይመስክራሉ

የመክፈቻ ጥያቄዎች

- ቅድስት ቤተክርስቲያን አንዲት ናት ስትባል ምን ማለት ነው?
- ቤተክርስቲያን ሐዋርያዊት ናት ስንል እንዴት ነው?

“ከሁሉ በላይ በምትሆን ሐዋርያት በሰበሰቧት በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን” የሚለው አንቀጸ ሃይማኖት፤ የእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን መታወቂያ የሆኑትን አምስት ባሕርያት ይዟል። እነርሱም፡ - አንዲት፣ ቅድስት፣ ሐዋርያዊት፣ የሁሉና በሁሉ ያለች፣ በሰማይም በምድርም ያለች የተባሉት ናቸው። እነርሱንም እንደሚከተለው በአጭሩ እንገልጻቸዋለን።

፪.፩ አንዲት ስለ መሆኗ

በመጀመርያ አንዲት የሚለው ቅጽል ለቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ መለያዋ ነው። ይህ ማለት ቤተክርስቲያን በውስጧ የሚፈጸሙት ምሥጢራት ሁሉ በቀኖናም ሆነ በነገረ ሃይማኖት በጥምቀትም ፤በቁርባንም በአጠቃላይ በአገልግሎት አሰጣጥ፡

. በአገር ውስጥ እና በውጪ አገር ያለችው ቅድስት ቤተክርስቲያን
. በትልቅ ሕንጻም ሆነ በትንሽ የጭቃ ጎጆ ብትሠራ

አንድ ዓይነት ጸጋ እና የመንፈስ ቅዱስ ልጅነት ታሰጣለች። ምክንያቱም ጌታችን አንዲት ቤተ ክርስያቲያንን እንጂ ሌላ አልመሠረተም። እርሷንም በደሙ ዋጅቶ በመመሥረት የራሱ አካል አደረጋት። እንግዲህ ክርስቶስ አንድ አካል አለው እንጂ ሁለት አካላት የሉትም። አንዷን ቤተ ክርስቲያን ከምሥራቅ ሌላውን ከምዕራብ ያቋቋመ አይደለም።እንዲያውም ጌታችን ከምሥራቅም ከምዕራብም ከሰሜንም ከደቡብም ያሉትን በጐቹን ሰብስቦ ሁሉንም አንድ መንጋ አንድ እረኛ እንዲሆኑ ለማድረግ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ መስርቷል (ማቴ ፳፪፤፲፩ ሉቃ ፲፫፥፳፬)።

ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን፡

. ቅርንጫፎቿ ብዙ ቢሆኑም
. በቦታና በጊዜም ቢራራቁም
. በብሔርና በቋንቋም ቢለያዩም

ከአንድ ወይን ግንድ እንደወጡ ቅርንጫፎች ይቆጠራሉ (ዮሐ.፲፭፥፩)፡ ፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በአንድ ተስፋ እንደተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤አንድጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት" ሲል አንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ እንዳለች ያመለክታል (ኤፌ.፬፥፭)። ምክንያቱም በጥቅሱ ላይ "አንድ አካል" የሚለው ቤተ ክርስቲያንን ነው። በአንድ ክርስቶስ የተጠመቅን የአንድ ክርስቶስ ሥጋና ደም የተቀበልን ሁሉ ከክርስቶስ ጋር ኅብረት አለን። ስለዚህም አንድ የክርስቶስ አካል እንሆናለን። በተለያየ ሀገርና ቦታ ያለችን ቤተክርስቲያን አንድ የሚያደርጋት፡-

- በመሠረተ እምነት አንድ መሆኗ
- በምሥጢራት እና ክብራቸው ላይ ተመሳሳይ እምነት በመኖሩ
- በቅዱስ ቁርባን ባላቸው አምልኮትና እምነት መመሳሰል ሲችሉ... የሚሉት ይጠቀሳሉ።
- ከዚህ በተጨማሪም በገጠርም ሆነ በከተማ ያለች ቤተ ክርስቲያን ክብር አንድ ነው፤
- ከወርቅም ትሠራ በሣር በመንፈስ ቅዱስ እስከ ከበረች አንዲት ናት።
- በአንዲት ጥምቀት ክርስትናን የተቀበሉም እንዲሁ በክርስቶስ አንድ ናቸው።

፪.፪ ቅድስት ስለ መሆኗ

ቤተክርስቲያን ቅድስት ናትና ጸሎታችንን "እምየ ቅድስት ቤተክርስቲያን" ብለን እንጀምራለን። ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫም በሰዓታት ድርሠቱ ላይ (ሰአሊ ለነ ቅድስት ቤተክርስቲያን መንፈሳዊት ዓውድ) ይላታል። ይህም ማለት እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሆይ የመንፈስ ቅዱስ አደባባይ ነሽና ለምኝልን፤ አማልጂን ማለት ነው።

ቤተክርስቲያን ስትመሠረት በጌታ ደም የነጻች ስለሆነ በእውነት ቅድስት ናት።የቅድስና ባለቤት መንፈስ ቅዱስ ባደረባት ጊዜ ፈጽሞ ቀድሷታል። የቅድስናና የጸጋው ሁሉ መዝገብ አድርጓታል። "እኔ ቅዱስ እንደሆንኩ

እናንተም ቅዱሳን ሁኑ" የሚለው የቅዱስ እግዚአብሔር ትእዛዝ ተፈጻሚነት የሚያገኘው በቅድስት ቤተክርስቲያን ነው ፩ኛጴጥሮስ ፩፥፲፭። ክርስቶስም ቤተ ክርስቲያኑን እንደ ቀደሳት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደሚከተለው ያስረዳናል። "ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እዲቀድሳት ስለ እርሷ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና አለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ" (ኤፌ ፭፥፳፭)። እንግዲህ በሙሽሪት የምትመሰል ቤተክርስቲያኑን በመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ለዘለአለም ቅድሰት አድርጎ ይጠብቃታል።

፪.፫ ሐዋርያዊት ስለ መሆኗ

ቅድስት ቤተክርስቲያን በሐዋርያት እግር ተተክታ ቃለ ወንጌልን በሚያምኑ አልቦ አይሁድ ወአልቦ አረማዊ (መልክዐ ኢየሱስ) እንዲል ሁሉንም ተቀብላ፣ አሳምናና መክራ በእምነት እንዲጸኑ የምታድርግ ናት። ሐዋርያትን በመተካት እስከ ዓለም ፍጻሜ በማስተማር ለመንግሥተ ሰማያት የምታበቃ በመሆኗ ከምድር እስከ ሰማይ የተዘረጋች ተቋም ናት። ቤተ ክርስቲያን የተሠራችው የመሥራቿን ማንነት በሚያውቁና በሚያምኑ፤ በዓይን ያዩ፣ በጆሮ የሰሙ፣ በዕጅ የዳሰሱ፣ የቃሉ መልእክተኞች በነበሩ፤ ትንሳኤውን በመሰከሩ በሐዋርያት ላይ ነው። ጌታ ሐዋርያትን በትምህርት በተአምራት አዘጋጅቶ የቤተክርስትያንን ሥራና ኃላፊነት አስረክበቧቸዋል። "እናንተን የሰማ እኔን ይሰማል" በማለት በቤተ ክርስትያን ላይ ሙሉ ሥልጣንን ሰጥቷቸዋል (ሉቃ ፲፥፲፮)። የእርሱ የሆነውን የነቢይነትን፣ የክህነትንና የንጉሥነትን ይህም ማለት የትምህርትን፣ የስርየተ ኃጢአትን፣ የጥበቃና የአስተዳደር ሥራና ሥልጣን ለእነርሱ አውርሷዋል።

ስለዚህም የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ላይ ተመስርታለች ብለን እናምናለን። ክርስቶስ የህያው እግዚያአብሔር ልጅ መሆኑን በመሰከረው በቅዱስ ጴጥሮስ እምነት ላይ ጌታ ቤተክርስቲያኑን እንደሠራ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻም እንደሰጠው ተጽፏል ማቴ፲፮፥፲፮። የኢትዮጲያ ኦርቶዶክዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስትያን ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ትባላለች። ቤተክርስቲያንናችን ጥምቀትን ሐዋርያት ከሾሟቸው ከሰባቱ ዲያቆናት አንዱ ከሆነው ከፊልጶስ በ፴፬ዓ.ም አግኝታለች። የሐዋ.፮፥፭

የቤት ሥራ

፩ .ለወላጆቻችሁ ስለ ቤተክርስቲያን አንዲት መሆንከ፣ቅድስት መሆን እና ሐዋርያዊት መሆን የተማራችሁትን አብራሩ።

፪.፬ የሁሉና በሁሉ ያለች ናት

ቅድስት ቤተክርስቲያን በሐዋርያት ከጽንፍ እስከ ጽንፍ በእግዚአብሔር አጋዥነት የተሰበከች ናት። በመላው ዓለም ሕዝብ ሁሉ የሚጽናናባት፣ ሕይወተ ሥጋ ሕይወተ ነፍስ የሚገኝባት፣ አምኖ ቃሏን ለሚሰማ ሁሉ “ወደ እኔ ኑ” ብላ የምትጣራ የሁሉም እናት ናት። ማንንም የማትልይ ኃጢአተኞችን (በደለኞችን) በንስሐ የምትጠራ፤ ራሱ መስራቿ ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ቃሉ “ከምሥራቅና ከምዕራብ ያሉ ሁሉ ከአብርሃም ጋር ወደ መንግሥተ ሰማያት ይገባሉ “ብሎ የተናገረላትዓለምአቀፋዊት ማቴ ፰፥፲፩፣ አማናዊት እና የሕይወት ቃል አብሳሪ ናት።

ይህ የሚያመለክተን ቤተክርስቲያን በሁሉም ቦታ ማለት በየአጥቢያው በየሀገሩ የምትገኝ ዓለም አቀፋዊት መሆኗ ነው። ጌታ ሐዋርያትን ከኢየሩሳሌም ጀምረው እስከ ዓለም ዳርቻ ወንጌልን እዲሰብኩ ባዘዛቸው

ጊዜ የቤተክርስቲያን ዓለም አቀፋዊነት ታወቀ የሐዋ.ሥራ ፩፥፰። ይህ ብቻ አይደለም ቤተክርስቲያን በቦታ ብቻ ሳይሆን በጊዜም አትወሰንም። ከሐዋርያት ጀምሮ ከዚያም በፊት በክርስቶስ ተስፋ የነበሩትን ሁሉ ይዞ ወደፊትም የሚመጡትን ሁሉ የምታጠቃልል ስለሆነች ቤተ ክርስቲያን በእውነት ኩላዊት ሁሉን አቀፍ ትባላለች። ከላይ በቤተ ክርስቲያን ትርጉም ላይ እንደተመለከትነው ቤተ ክርስቲያን በምድር ብቻ ያለችው ሳትሆን በሰማያዊ ስፍራ የምትገኘውን የክርስቶስን ቤተሰቦች ጎብረትያጠቃለለች ናት። ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ኩላዊነት በሰማይም፣ በምድርም፣ ጥንትም፣ ዛሬም፣ ወደ ፊትም ያሉትንና የሚመጡትን ሁሉ ያካትታል።

ቤተ ክርስቲያን ኩላዊት ስለሆነች ተልዕኮዋና አገልግሎቷ ለሁሉም ወገኖች በሁሉም ቋንቋ ሆኖ እናገኛዋለን።በሁሉም አገር ያሉት አብያተ ክርስቲያን አገልግሎታቸው የአንድ ክርስቶስ ስለሆነ እንደተበታተኑ እንደ ተለያዩ ነገሮች አይቆጠሩም። ምክንያቱም በሰማይም በምድርም የሚገኙት ሁሉ በአንድ የክርስቶስ አማኝነታቸው፣ በመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ፣ በሥራና በጸሎት ይገናኛሉ። ስለዚህም ኩላዊነትና አንድነት የተገናዘቡና የማይለያዩ የቤተ ክርስቲያን መታወቂያዎች ናቸው።

፪.፭ በሰማይም በምድርም ያለች ናት

እግዚአብሔር አምላክ ሙሴ ደብተራ አሪትን በሚሠራበት ጊዜ በሰማያዊት መቅደስ አምሳል እንዲሠራ አዘዘው ዘፀ ፳፭፥፰ ፳፮፥፴። ይህም ቅድስት ቤተክርስቲያን ሰማያዊት መሆኗን ይገልፃል። “በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር” ብለን እንድንጸልይ ጌታችን ያስተማረው ይህንን ያመላክታል። ስለዚህ ቅድስት ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ያለች የእግዚአብሔር መንግሥት መሆኗን በዚህ እናምናለን። በዚህች ቤተክርስቲያን ሁነን የምንሠራው መልካም ሥራ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ያደርሰናል፤ ዘለዓለማዊ ሕይወትም እናገኝበታለን።

በዘመነ ሐዋርያት የነበረችው የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን አባላት በአህዛብ መካከል ወንጌልን ሰብከዋል።በዓላውያን ነገሥታት ፊት ስለ ክርስቶስ በመመስከር በልዩ ልዩ ተጋድሎና ትሩፋት ከኖሩ በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ድልን በመቀዳጀት በገነት ካለች የቅዱሳን ጎብረት ተደምረዋል። ገላ. ፬፥፳፯ ሉቃ ፳፫፥፵፫።

በሁለተኛ ደረጃ የምትገኘው ቤተ ክርስቲያን ከዘመነ ሐዋርያት በኋላ በምድር ላይ የነበረችው፣ያለቸውና የምትኖረው ናት። እርሷም የመጀመሪያዋን ቤተ ክርስቲያን ፈለግ በመከተል የክርስቶስን መስቀል ተሸክማ በፈተናና በተጋድሎ ትገኛለች። የውጪ ጠላቶቿ እያሳደዷት የውስጥ ባለጋራዎቿ እየተቃወሟት ብትገኝም የእግዚአብሔር ረድኤት ሳይለያት በመንፈስ ቅዱስ እየተጽናናች ተጠብቃ ትኖራለች። በዓለም ውስጥ ያለቸው ቤተክርስቲያን ከዓለም ስላልሆነች በዚህ ምድር ላይ እንደ እንግዳ መጻተኛ እንደ ስደተኛም ለመኖር ትገደዳለች።

ማጠቃለያ

-ቤተክርስቲያን አምስት ባሕርያት አሏት “አንዲት” “ቅድስት“ ”እና “ሐዋርያዊት” “የሁሉና በሁሉ ያለች” እና “በሰማይም በምድርም ያለች መሆኗነው። አንዲት ቤተክርስቲያን እነዚህን ባሕርያት ካላሟላች ቤተ ክርስቲያን አትባልም።

-ተማሪዎች እናንተም አምስቱንም የቤተክርስቲያንን ባሕርያት አውቃችሁ ማሳወቅ ይጠበቅባችኋል።

የመልመጃ ጥያቄዎች

ለየሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ/ሽ

፩. ቤተክርስቲያን ሦስት ባሕርያት አሏት?

፪. ቤተክርስቲያን የምትገኘው በምድር ብቻ ነው?

፫. በወርቅ በእንቁ የተሠራች ቤተክርስቲያን በሳር በጭቃ ከተሠራችው ቤተክርስቲያን የበለጠ ክብር አላት?

ለየሚከተሉትን ጥያቄዎች አብራራ/ሪ

፩. ቤተክርስቲያን አንዲት ናት ስንል ምን ማለታችን ነው?

፪. ቤተክርስቲያን የሁሉና በሁሉ ያለች ናት ስንል ምን ማለታችን ነው?

ምዕራፍ ሦስት

የቤተክርስቲያን ስያሜ በሊቃውንት

ዓላማ

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ

- ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ቅድስት ቤተክርስቲያንን ምን ብለው ይጠሩ እንደነበር ይረዳሉ
- የሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን ለቤተክርስቲያን የነበራቸውን ምልከታ ያውቃሉ

የመክፈቻ ጥያቄዎች

- ቅድስት ቤተክርስቲያን የፀጋው ግምጃ ቤት በመባል ትጠራለች ስለምን አብራሩ?

፫.፩ ቤተክርስቲያን ዘእግዚአብሔር

ከቤተ ክርስቲያን ስያሜዎች አንዱ ቤተክርስቲያን ዘእግዚአብሔር የሚለው ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በተለያዩ ቦታዎች ቤተ ክርስቲያንን ቤተ ክርስቲያን ዘክርስቶስ (የክርስቶስ ቤተክርስቲያን)፣ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን እያለ ጠርቷታል። ለሮም ምእመናን በላከው መልዕክቱ ላይ ሲሰናበታቸው "የክርስቶስ አቢያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል" ብሎአል ሮሜ ፲፮፥፲፮። ለቆሮንቶስ ምእመናንም "በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን..."በማለት ጽፏል ፩ኛቆሮ ፩፥፪። በሌሎችም መልእክቶቹ በተደጋጋሚ ተጠቅሞበታል። ፪ኛ ቆሮ ፩፥፩ ገላ ፩፥፲፫ ፩ኛ ተሰ ፪፥፲፬ ፪ኛ ተሰ ፩፥፬ ፩ኛ ጢሞ ፫፥፭ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አጠራር ለምን እንደተጠቀመበት በመልእክቶቹ ላይ ተርጉሞታል። ለኤፌሶን ምእመናን በጻፈው መልእክቱ እንደገለጸው የቤተ ክርስትያን ራሷ፣ ገዥዋና አዳኟ ክርስቶስ ነው ኤፌ ፭፥፩። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ዘክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ዘእግዚአብሔር ተብላ ትጠራለች።

፫.፪ ቤተክርስቲያን

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል ሦስት ፍቺ አለው። አንደኛው በክርስቶስ አምነው የተጠመቁ የምእመናን አንድነት ወይም ማኅበር ምእመናን ነው። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ ፩፡ ማቴ.፲፮፥፲፯፣የሐዋ.፳፥፳፰። በብሉይ ኪዳን የነበሩ ሕዝበ እግዚአብሔር ቤተ እስራኤል ተብለው ይጠሩ እንደነበሩ በሐዲስ ኪዳን ያሉ ሕዝበ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ተብለዋል። ይህም ሕዝበ ክርስቲያን ነገደ ክርስቲያን ማለት ነው።

ሁለተኛው አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸምበት ምእመናን የሚሰበሰቡበት ሕንፃ ቤተክርስቲያን ነው። ሐመረ ኖኅ ሃይመተ አብርሃም ደብተራ ኦሪትና መቅደሰ ሰሎሞን ለቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ሆነው መሥዋዕት ሲሠዋባቸው አምልኮተ እግዚአብሔር ሲፈጸምባቸውና ስመ እግዚአብሔር ሲቀደስባቸው ኖረዋል።

እነዚህ ሁሉ ካለፉ በኋላ የቤተክርስቲያን መሠረትና ራስ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አማናዊት ቤተክርስቲያንን በደሙ መሠረተ። የቤተክርስቲያን አባቶች በጸሎተ ሃይማኖት ውስጥ በወሰኑት መሠረት ቤተክርስቲያን ‹‹አንዲት፣ ቅድስት፣ በሁሉ ዘንድ ያለች፣ሐዋርያት የሰበሰቧት››ትባላለች (ጸሎተ ሃይማኖት)

ቤተክርስቲያን፡-

- ማኅደረ እግዚአብሔር ናት
- የትምህርት የጸሎትና የአምልኮት ቤት ናት
- የኃጢአት ማስተስርያ መስገጃና መማጸኛ ናት
- ወንጌል ይሰበክባታል ቅዱስ ቁርባን ይቀርብባታል
- በጥምቀት ልጅነት ይሰጥባታል
- የክርስቲያኖች አጽም ያርፍባታል

የክፍል ሥራ

፩.የቤተክርስቲያንን ስያሜዎችን ካለፈው ትምህርታቸሁ አስታውሳችሁ ለመምራችሁ ንገሩ። መምህር ተማሪዎች የታዘዙትን ይሠሩ ዘንድ እርዷቸው።

፫.፫ ቤተ ክርስቲያን ዘክርስቶስ

ጌታችን አምላካች መድኃኒታችን ኢያሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ሲል ያላደረገው ነገር ምንም የለም። ከሰማየ ሰማያት ወረደ ፤ከድንግል ማርያም ያለ ዘርዓ ብዕሲ ተወለደ፤ በዕለተ ዓርብ በመልእልተ መስቀል ተሰቅሎ ሞተ፤ ተቀበረ። ይህንን ሁሉ ለመፈጸም ከልዕልናው ሊወርድ የቻለበት ምክንያት የሰው ልጆችን በመውደዱ ነው። "ፍቅር ሰሀቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ" እንዲል ቅዳሴ ማርያም። ይህ ሁሉ ቸርነት የበዛበት ታላቅና

አባታዊ ርኅራሄ፤ ያደረገልንን ውለታ በእጅጉ እንድናስብና ወደ እርሱ እንድንቀርብ የሚቀሰቅስ ኃይል ያለው መሆኑን እንድንገነዘብ ያደርጋል።

፫.፬ ማኅደረ እግዚእ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ማደርያ ናት።አባቶቻችን በትውፊት ካቆዩልን አንዱ በቤተመቅደስ ፊት ለፊት ቆመን በምንሰግድበት ጊዜ እያማተብን “ሰላም ለኪ ቤተ ክርስቲያን ማኅደረ አብ ፤ማኅደረ ወልድ ፤ማኅደረ መንፈስ ቅዱስ” ብለን የምንሰግድበት ሥርዓት ነው። ቅዱስ ዳዊትም በመዝሙሩ”ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ” ብሏል መዝ ፻፳፩፥፩። ይልቁንም ደግሞ “ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።”የሚለው አምላካዊ ቃል ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ማደሪያ መኖሪያ መሆኗን ያረጋግጥልናልማቴ ፲፰፥፳። ስለዚህምየእግዚአብሔር ማደሪያ (ማኅደረ እግዚእ) እየተባለች ትጠራለች ፩ኛ ቆሮ ፲፫፥፲፮።

፫.፭ የጸጋው ግምጃ ቤት የምሕረቱ ማኅደር

ሁሉን በሁሉ የሚያደርገው አንዱ እግዚአብሔር ልዩ ልዩ የሆኑ የጸጋ ስጦታዎች አሉት። በእውቀት የመናገር ጥበብ፣ የመፈወስ፣ የመተርጎም፣ ወዘተ... ስጦታዎች ከእግዚአብሔር ይሰጣሉ። ይህን ሁሉ አንዱ መንፈስ ቅዱስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ እያካፈለ ያደርጋል ፩ኛቆሮ፲፪፥፩። እነዚህን የጸጋ ስጦታዎች ለማግኘት በመጀመሪያ በወንጌል አምኖ በመጠመቅ ወደ ቤተክርስቲያን መግባትና በውስጧም መኖር ያስፈልጋል። ልዩ የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ (ጸጋ) የሚሰጠው ከእግዚአብሔር ቢሆንም ከቤተክርስቲያን ውጪ ግን አይገኝም።

ለምሳሌ የኃጢአት ስርየት ወደ ቤተክርስቲያን ቀርበው በንስሐ ሲመለሱ፤የእግዚአብሔር የልጅነት ጸጋ በቤተክርስቲያን ተጠምቀው በቅብዓ ሜሮን ሲከብሩ፤ የባል እና ሚስት አንድ የመሆን ጸጋ

በሥርዓተ ተክሊል በክርስቶስ ሥጋ እና ደም ሲታተሙ፤ ወዘተ... ነው የሚገኘው። ስለዚህ ቤተክርስቲያን የጸጋው ሁሉ ግምጃ ቤት እና ጸጋው የሚታደልባትም ቦታ ናት። ያለ ጸጋ የእግዚአብሔር ድኅነት የለም። ጸጋ እግዚአብሔርን ማግኘት የሚቻለው ደግሞ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን በመሳተፍ ነው። ምስጢራተ ቤተክርስቲያንን የምንፈጽምባት፤ ጸጋ እግዚአብሔርን የምንቀበልባት ደግሞ ቤተክርስቲያን ናት። "እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።" በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የጸጋው ግምጃ ቤት መሆኗን አረጋግጦልናል እና በዚህ ስም ትጠራለች ዕብ ፬፥፲፮።

፫.፮ ቤተክርስቲያን ሠርክ ሐዲስ

ቤተክርስቲያን ሁሌ ሐዲስ ሁልጊዜም የማትሰለች እና አማናዊት መማፀኛ የእግዚአብሔር ጸጋና በረከት የፈሰሰበት (የሞላባት) በመሆኗ ሁልጊዜ ሐዲስ ትባላለች። ምክንያቱም ቅድስት ቤተክርስቲያን ክርስትና ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ "ቅድስት ቤተክርስቲያንን ሁላችን ሰላም እንበላት እንሳለማት (እንሳማት)" እያሉ ከጥንት የነበሩት አባቶቻችን በእንደዚህ ዓይነት ፍቅር ሰላምታ ያቀርቡለት ነበር። በዚህ ዘመን ያለው ትውልድም ይህንን የአባቶቹንምስጋናና ለቅድስት ቤተክርስቲያን የሰጡትን ክብር ማስቀጠል ግዴታው ነው። በመሆኑምበ"ዘመናዊነት እና ሥልጣኔ" ሰበብላለው ተጽዕኖ ሳይበገሩ መንፈሳዊነቱን በማበርታት የአባቶቹን አደራ ሊወጣ ይገባዋል። "አባትህን ጠይቅ ያስታውቅሀል ሽማግሌዎች ጠይቅ ይነግርሩሀል" ኦሪት ዘዳግም ፴፪፥፯ እንዲል፤ የዘመኑም ትውልድ ይህን ማስጠቀጠልአለበት፤ ይህን ባለማድረጋቸው በታሪክ የተወቀሱ ትውልዶች ነበሩና።

-ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ማደርያ ናት። ይሄን ስሟ እና ግብርዋ በተለያዩ ቅዱሳን አባቶች ተገልጧል።እነዚህም ተመልክተናል

ቤተክርስቲያን የጸጋው ግምጃ ቤት ቤተክርስቲያን ዘ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ዘእግዚአብሔር ተብላ ትታወቃለች፡፡

- ተማሪዎች እናንተም ከዚህች የጸጋዎች መፍለቂያ ከሆነች መልካም ምንጭ ተጠግታችሁ መልካም ፡ ንጹህ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ልትጠጡ ይገባል፡

የማጠቃለያ ጥያቄዎች

፩.በቤተክርስቲያን ከሚሠጡ አገልግሎቶች መሀከል ሦስቱን ጥቀስ/ሺ

፪.ቤተክርስቲያን የጸጋው ግምጃ ቤት ናት ስንል ምን ማለታችን ነው ?

፫. ወደ ቤተክርስቲያንን ስንገባ ምን እያልን ነው እምንገባው ?

የሚከተሉትን ጥያቄዎች እውነት ወይም ሀሰት በማለት መልስ ስጪ/ጥ

፩.ቤተክርስቲያን ዘክርስተቶስ ተብላ እምትጠራው መስራቿ እና ባለ ቤቷ ክርስቶስ ስለ ሆነ ነው?

፪.ከእግዚአብሔር የሚሰጡ ጸጋዎችን ለመቀበል መጀምርያ ማመን እና መጠመቅ ያስፈልጋል ?

፫.የክርስቲያኖች አፅም የሚያርፈው ከቤተክርስቲያን ቅጥር ውጪ ነው ?

ምዕራፍ አራት

የቤተ ክርስቲያን እድሜ

ዓላማ
ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ

ፀ ቤተክርስቲያን ከዓለመ መላእክት ጀምሮ የነበራትን እድሜ ይረዳሉ
ፀ ሦስቱን የቤተክርስቲያን እድሜ ለይተው ይጠቅሳሉ

የመክፈቻ ጥያቄዎች

ፀ ቤተክርስቲያን በዓለመ መላእክት አለች ሲባል ምን ማለት ነው?

አማናዊት ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው ግንቦት ፲፮ቀን ፴፫ ዓ.ም እንደሆነ ተጽፏል። ጊዜውም በዓለ ሃምሳ ነበር። በዚህ ጊዜ የበዓለ ሃምሳን በዓል ለማክበር ቤተ እግዚአብሔርን ለመሳለም በመጡት አይሁድ መካከል በማርቆስ እናት በማርያም ቤት ተቀምጠው የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ለመልበስ በተስፋ ይጠብቁ ለነበሩት ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ወርዶ ኃይልን ሰጣቸው። ከዚህ በኃላ ሐዋርያትም ማስተማር እንደ ጀመሩ በሐዋ ፪፥፩ ተመዝግቦ እናየዋለን።

፪.፩ በዓለመ መላእክት

በክርስትና ታሪክ ውስጥ መላአክት የእግዚአብሔር ምሥጢር ተካፋዮች እና የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው።በመጀመሪያ አምላክ ሰው ሊሆን ነው ብሎ የተናገረ የእግዚአብሔር መልአክ ነው። በተወለደም ጊዜ የዓለም መድኃኒት ተወለደ ብሎ መጀመርያ ለሰው ልጆች የሰበከ የእግዚብሔር መልአክ ነው። በሥነ ፍጥረት ትምህርት እንደተማርነው መላእክት በዕለተ እሑድ የተፈጠሩ እና በሰማያት እግዚአብሔርን ዘወትር ያለማቋረጥ ቅዱስ ቅዱስቅዱስእያሉ በእንድነት የሚያመሰግኑ ረቂቃን መንፈሳውያን ፍጥረታት ናቸው። የተፈጥሮ ክብራቸው እኩል ቢሆንም በነገድ በነገዳቸው አለቆች አሏቸው። አገልግሎታቸውም በየ ነገዳቸው የተከፋፈለ ነው። በአጠቃላይም የእግዚአብሔርን ምሕረት፣ቁጣ ወይም የማስጠንቀቂ መልእክት ወደ ሰው ፤ የሰውንም ልመና ወደ እግዚአብሔር በማድረስ ያገለግላሉ። በአምልኮት፣ በስብሐተ እግዚአብሔር እና ይህን በመሳሰለው ሁሉ አንድ በመሆናቸው ይህ አንድነታቸው ወይም ኅብረታቸው ቤተ ክርስቲያን ይባላል።

ከመላእክት አለቆች ወገን የነበረው ሳጥናኤል ከአምልኮተ እግዚአብሔር በተናወጸበት ጥርጥር እና ክህደትን ባመነጨበት ጊዜ ከመላእክት አንድነት (ከቤተ ክርስቲያን) ተለየ፤ በክህደት የተባበሩት መላእክትም እንዲሁ ንጽሕት ከሆነችው ከመላእክት ማኅበር አብረውት ተለዩ። ከዚያን ጊዜ

በኋላ እርኩሳን መናፈስት (ሰይጣናት) ተብለው በመጠራት ከክብራቸው ተዋርደው ወደ ምድረ ፋይድ ወረዱ። እስከ ዓለመም ፍጻሜ ድረስ የክፋት ምንጭ በመሆን እና ሰውን አሳስተው ከእግዚአብሔር መንግሥት እንዲለይ ለማድረግ በመውጣት እና በመውረድ ይኖራሉ።

አዳምም ከተፈጠረ በኋላ በአምልኮት እና እግዚአብሔርን በማመስገን ከቅዱሳን መላእክት ጋር በኅብረት ይኖር ነበር። ሆኖም ግን አዳም ሕገ እግግዚአብሔርን ከጣሰ በኋላ ያበመጀመሪያ የነበረው ኅብረት ተቋርጦ ቆይቷል። ጌታ በተወለደባት የማዳን ሥራው በተጀመረባት ሌሊት ደግሞ ተቋርጦ የነበረው ኅብረት እንደገና ተመስርቶ ሰው እና መላእክት "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ስምረቱ ለሰብእ" በማለት በአንድነት ዘምረዋል።(ሉቃ ፪፥፲፬) ከዚህም የምንረዳው የቤተክርስቲያን እድሜ የሚጀምረው ከመላዕክት መፈጠር ጋርበዕለተ እሁድ መሆኑን ነው።

፪.፪ የደጋግ አበው አንድነት

እግዚአብሔር አምላክ ከሌሎቹ ፍጥረታት ሁሉ በተለየ ሁኔታ የሰውን ልጅ በራሱ አርአያ እና ምሳሌ አድርጎ በመፍጠር ከባረከው በኋላ ለቀሩትም ምድራዊፍጥረታት የበላይ ገዢ እንዲሆን ሾመው። ሰው በተፈጥሮው ነጻ ፈቃድ፣ ክፉ እና ደግ የሚለይበት ሙሉ አእምሮ ያለው ሲሆን ፈጣሪውን የሚያስታውስበት አንዲት ትዕዛዝ ተሰጥቶት ነበር።ይኽውም "ከዕፀ በለስ እንዳትበላ" የሚል ነው። አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መምህራን ይህን ትዕዛዝ የፍቅር ሕግ በማለት ይጠሩታል።

እግዚአብሔር አምላክ የሰውን ልጅ እንዳይሞት ፈልጎ ይህን ትእዛዝ ሰጠው። ነገር ግን አዳም ከሚወደው ከእግዚአብሔር ይልቅ የሚያሳስተውን የእባብን ምክር ሰምቶ ዕፀ በለስን በመብላቱ ሞትን በራሱ ላይ አመጣ።ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የልጅነት ጸጋ ተገፈፈ፤ ከክብሩ ተዋርዶ ከገነት ተባረረ።

እስከ ጊዜውም ድረስ ወደምድረ ፋይድ በመውረድ ጥሮ ግሮ በወዙ ይበላ ዘንድ ተፈረደበት። ይህንንም ቅጣት ከእርሱ የተወለዱ የልጅ ልጆቹ ሁሉ በውርስ ተካፈሉት። የሰው ልጆችም የኃጢአት ዝንባሌ እየጨመረ በመሄዱ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረው ልዩነት እየሰፋ ሄደ። ብዙዎችም የፈጠራቸውን እግዚአብሔርን ዘንግተው በተፈጥሮ ከእነርሱ በታች የሆኑ በሰማይ እና በምድር ያሉትን ግዑዛን ፍጥረታትን ቅርፅ (ምስል) ማምለክ ጀመሩ። ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ አዳም ንስሓ በገባ ጊዜ የሰጠውን የተስፋ ቃል በማሰብ የሰው ዘር ፈጽሞ እንዳይጠፋ በየወቅቱ ለበረከት የሚሆኑ አንዳንድ ሰዎችን አተረፈ። ከአዳም ጀምሮ እስከ ኖኅ ድረስ ያሉት በዘፍጥረት ምዕራፍ አምስት ላይ የተዘረዘሩት አባቶች አሥሩ አበው በመባል ይጠራሉ። ከነዚህም ውስጥ በትውልድ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ ሲያልን እንዳያይ ሳይሞት ተሰወረ። ልጁ ማቱሳላም ከሰው ልጆች ይልቅ ረጅም ዕድሜን (፱፻፷፱ 969 ዓመት) ኖረ። ዓለም በንፍር ውኃ ከጠፋችበት ከኖኅ ዘመን በኋላ እንደዚሁ በሴም በኩል ፲ ትውልድ ቆጥረን አብርሃምን እናገኛለን። አብርሃም በትወልዱ ሶሪያዊ ሲሆን እርሱ ብቻ በፍጹም ልቦናው እግዚአብሔርን የሰማይና የምድር አምላክ መሆኑን ተረድቶ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ፈጥሮ አልፏል። የእነዚህና የመሳሰሉት አበው ጎብረት ቤተክርስቲያን ትባላለች።

፬.፫ የክርስቲያኖች አንድነት

የጥንቱ ክርስቲያኖች በአንድነት ይኖሩ ነበረ። ገንዘባቸውንም ፤የሚመገቡትንም ሆነ ማንኛውም ነገር ያገኙትን ሁሉ በጋራ ይጠቀሙ ነበረ የሐዋ ፪፥፵፭። ክርስቲያኖች በአንድነት በፍቅር መኖር ይጠቅማቸዋል። ፍቅር ካለ እግዚአብሔር አለ፤ እግዚአብሔር ካለ ደግሞ ጸጋና በረከት፣ ይቅርታና ምሕረት ይኖራል። ቤተክርስቲያን ማለት የክርስቲያን ቤት የክርስትና መሰባሰቢያ የክርስትያን መገናኛ ማለት ነውና። በአንድነት መገኘት እንደ ሐዋርያት ለክብር ያበቃል። ቅዱሳን ሐዋርያት በጽርሐ

ጽዮን ጸጋመንፈስ ቅዱስን እንደተቀበሉ፤ እኛም እንደ ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ጸጋእንድንቀበል ዘወትር በቤተክርስቲያን መገኘት አለብን፡፡

ማጠቃለያ

-ምስጋና የተጀመረው በመላእክት ነው፡፡ ይህም ማለት የመጀመርያዋ ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው መላእክት ምስጋና ሲጀምሩ በዕለተ እሑድ ነው፡፡

-ዛሬም እኛም ከቅዱሳን መላእክት በመማር ዘወትር የእግዚአብሔርን ምስጋና ማስታጎል የለብንም፡፡

የክለሳ ጥያቄ

፩.በአማናዊት የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እና በዓለመ መላእክት ጊዜ በነበረችው ቤተክርስቲያን ያለውን ልዩነት እና አንድነት አብራሩ፡፡

፪.የደጋግ አበው አንድነት ስንል ምን ማለታችን ነው?

ምዕራፍ አምስት

የቤተክርስቲያን ምሳሌ በብሉይ ኪዳን

ዓላማ
ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ሲያጠናቅቁ

ፏ የቅድስት ቤተክርስቲያንን ምሳሌዎች ከብሉይና ከሐዲስ ኪዳን ለይተው ያውቃሉ
ፏ በቤተክርስቲያን ምሳሌዎች ውስጥ የቤተክርስቲያንን ልዕልና ይረዳሉ



የመክፈቻ ጥያቄዎች

ፏ.፩ የቤተክርስቲያን ምሳሌ በብሉይ ኪዳን

፮.፩.፩ ጠፈር

ቀና ብለን ወደላይ ስንመለከት የምንመለከተው ውኃ አዘል ሰማይ ሲሆን፣የሥነ ፍጥረት ትምህርታችን ጠፈር ይለዋል። በዚህ መሠረት ቤተክርስቲያን በጠፈር ትመሰላለች።

. ጠፈርን ቀን ከሌሊት በመፈራረቅ ብርሃን እንደማይለዩት ቤተክርቲያንም እንዲሁ ቀን ከሌሊት በመፈራረቅ ብርሃናዊያን ቅዱሳን መላእክት አይለዩአትም።

. ጠፈር በሰማይ እንዳለ ሁሉ ቤተክርስቲያንም ምድራዊት ብቻ ያይደለች ሰማያዊትም ነች

. ጠፈር ከምድር ከፍ ያለ እንደሆነ ቤተክርስቲያንም ከምድራዊ ጠባይ ተለይታ በክብር ከፍ ባለ ልዕልና ደምቃ የምትኖር ለመሆኗ ምሳሌ ነው።

፮.፩.፪ ገነት

ገነት መንግሥተ ሰማያት በዳግም ምጽአት እስክትከፈት ድረስ ቅዱሳን የሚቆዩባት ቅድስት ሥፍራ ነች።ከመዓዛዋ ጋር የልምላሜዋ ውበት ሲደመር ለሕይወት ልዩ ተመስጦን ይፈጥራል። በገነት ሐዘን ጨርሶ አድራሻው የለም። በመንፈሳዊ ደስታ ተመልታለች በጽድቅ ተወስነው በምድር ሐዘን ያንገላታቸውን የናፈቋትን ደስታ የሚወጡት በገነት ነው። የተጎዱም ዋጋቸውን በእጥፍ እንደ አልአዛር ያገኙባታል ሉቃ ፲፮፥፲፱።

. ቤተክርስቲያን የገነት ምሳሌ ነች በገነት ልዩ ልምላሜ እንዳለ ሁሉ በቤተክርስቲያን ልምላሜ ጽድቅ አለ።በተጨማሪም በቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ያሉዕፀዋት ሁሉ ያለምክንያት አልተቀመጡም፤ቤተክቲያን የገነት ምሳሌ ስለሆነች ነው። ዕፀዋቱን ስንመለከት ልምላሜ ገነትን እንድናስብ ያደርጋል።

, በገነት ደስታ እንጂ ሐዘን እንደሌለ በቤተክርስቲያን ደስታ መንፈሳዊ አለ። በንስሐ በደላችን ሲደመሰስ፤በክርስቶስ ሥጋና ደም ስንቀደስ፤ ጋብቻን በተክሊል ስንፈጸም፤ከካህናቱ ቡራኬ ስንቀበል፤እንደቅዱሳን መላእክት ስንዘምር፤ በእግዚአብሔር ቃል ውስጣችን ሲረካ ይህንና

የመሳሰሉት ስንፈጸም ሕይወታችን በመዓዛ መንፈስ ቅዱስ ይረካል። ሐዘናችን በደስታ ይለወጣል። መንፈሳዊ ሰው ላዩ የጠወለገ ይመስላል እንጂ ውስጡ ግን በእግዚአብሔር ሰላም ደስተኛ ነው መዝ ፷፫፥፯።

፭.፩.፫ የአብርሃም ድንኳን

አብርሃም ሥላሴን በእንግድነት የተቀበለባት ድንኳን ቤቱ የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት ዘፍ./፲፰/።

. ሥላሴ በእንግድነት በአብርሃምቤት/ድንኳን/ እንደተገኙ በቤተክርስቲያን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ያድራሉ።

. በቤተ- አብርሃም ውስጥ አብርሃም ምሥጢረ ሥላሴን እንደተማረ በቤተ ክርስቲያንም ምሥጢረ ሥላሴ ይነገራልና።

. በቤተ-አብርሃም ድሀ፣ ሀብታም፣ ነጭ ፣ጥቁር፣ የተማረ ፣ያልተማረ፣ ኃጥእ፣ ጻድቅ ሳትል እንግዳ እንደተቀበለች ቤተክርስቲያንም ያለ አድሎ ሁሉን በእኩል ዓይን ትቀበላለች።

. ቤተ-አብርሃም ምግበ ሥጋ ይመገቡባት እንደነበር በቤተክርስቲያንም ሥጋ ወደሙ ቃለ እግዚአብሔር ይገኛል።

፭.፩.፬ ቤቴል

ያዕቆብ በፍኖት ሎዛ ምሥጥር እግዚአብሔር ያየባት ቤትኤል ናት። በዚህ ቦታ ላይ መላእክተ እግዚአብሔር ሲወጡባት እና ሲወርዱባት ያየት የብርሀን መሰላል የእመቤታችንና የቤተክርስትያን ምሳሌ ናት። ዛሬም በቤተክርስትያን መላእክት የምእመናን ጸሎት ትሩፋት ይዘው ወደ እግዚአብሔር፤ከእግዚአብሔር ደግሞ ለምእመናን ረድኤት እና ምሕረት ለማምጣት ከመውጣት ከመውረድ አላቋረጡምና።

፭.፩.፭ ደብተራ ኦሪት

. ደብተራ ኦሪት ደብተራ ማለት ድንኳን ማለት ነው፣ ደብተራ ኦሪትም ታቦተ ሕግ የኖረባት ሌዋውያን ሕግ የተማሩባትና ሥርዓተ አምልኮ

የፈጸሙባት ድንኳን ናት። በዚህች ድንኳን ሰውና እግዚብሔር ይገናኙባት ስለነበር መገናኛ ተብላለች /ዘዳ ፴፫፥፯-፲/። ደብተራ ኦሪት በሙሴ ዘመን በብዙ ጌጥ የተሠራች ነበረች። ነቢዩ ዳዊትም ታቦት አኑሮባት ለ፬፻፹ 480 ዓመታት አገልግሎት ስትሰጥ ቆይታለች/፪ኛ ሳሙ ፮፥፲-፳፫/። በቤተ ክርስቲያንም ሰውና እግዚአብሔር ይገናኙባታል፤ ታቦተ ሕጉ ይኖርባታል።

፭.፩.፮ ደብረ ሲና

ደብረ ሲና ሙሴ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ጾሞ ጸልዮ ሕገ እግዚአብሔር የተጻፈበትን ጽላት የተቀበለበት፤ እስራኤል ዘሥጋ ሕገበ እግዚአብሔር የተባሉበት ተራራ ናት። ይህቺውም እስራኤል ዘነፍስ /ክርስቲያኖች/ በጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ተወልደው ውሉደ እግዚአብሔር የተባሉባት፤ ርስት እግዚአብሔር መንግሥተ ሰማትን ለሚወርሱባት፤ ለቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት/ዘጽ ፳፬፥፲፪-፲፰/።

፭.፩.፯ ምኩራብ

ኩራብ እንደ ደብተራ ኦሪት ሁሉ እግዚአብሔር የተመለከበት ሕንፃ ነው። ምኩራብ የተሠራው ከልደተ ክርስቶስ በፊት በ956 /በ4544 ዓመተ ዓለም/ በሰሎሞን ነበር። ነቢዩ ቅዱስ ዳዊት ቤተመቅደስን ለመሥራት ብዙ ጊዜ ቢመኝም በእግዚአብሔር ፈቃድ በልጁ በሰሎሞን ባማረና በተዋበ አሠራር ተሠርቶ ታቦተ ጽዮንን አስገብተው ካህናት ሲያገለግሉበት ቆይተዋል። ይህ ቤተ መቅደስ በናቡከደነጾር ከክርስቶስ ልደት በፊት በ586 /በ4914 ዓመተ ዓለም/ ቤተ እሥራኤል ወደ ባቢሎን ሲማረኩ ፈራረሰ፡ ፡ /ነህ ፯፬፥፲/ ከእስራኤልያውያን ከምርኮ መመለስ በኋላም በዘሩባቤል ዘመን በድጋሚ ተሠርቷል። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም “ኢትግበሩ ቤተ አቡየ ቤተ ምሥያጥ” ብሎ ሻጮችንና ለዋጮችን አባረረ /ማቴ፳፩፥፲፪/። ምኩራብ የቤተክርስቲያንምሳሌ ነው፤ ቤተክርስቲያን አማናዊት የእግዚአብሔር ማደሪያ ቤቱ ናትና ።

፮.፩.፰ የኖኅ መርከብ

ሐመረ ኖኅ /የኖኅ መርከብ/ የሰው ልጆች በምድር ላይ እየበዙ በሄዱ ጊዜ እግዚአብሔርን በድለው ነበር። በዚሁ ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው (በሕገ እግዚአብሔር የሚመራ) ኖኅ ብቻ ነበር። ሰዎች በበደላቸው ምክንያት በማየ አይህ /በንፍር ውኃ/ ሲደመሰሱ ኖኅ ግን ስምንት ራሱን ይዞ ወደ መርከብ ካስገባቸው እንስሳት አራዊትና አዕዋፍ እንደየወገናቸው ጋር ከጥፋት ድነዋል። የኖህ መርከብ የእግዚአብሔር ሰዎች ከጥፋት የዳኑበት ስትሆን ክርስቲያኖች ከባህር እሳት፤ከሞት ነፍስና ከግብርናተ ዲያብሎስ የምታድን የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት ዘፍ ፮፥፭-፰፪።

. በኖኅ መርከብ ውስጥ የነበሩት አውሬዎች በውጡ እና በገቡ ጊዜ ከአውሬነታቸው
አልተለወጡም፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡ እና የሚወጡ ግን ቀማኛው መጽዋች፣ ዘማዊው ድንግል ይሆናል። በወጡ እና በገቡ ሲል በቤተክርስቲያንም በዓለምም ለማለት ነው።

, ጻድቁ ኖኅ ያዘጋጃት መርከብ ሦስት ክፍሎች ነበሯት። ዛሬም ቤተ ክርስቲያን ሦስት ክፍሎች አሏት።ቅኔማኅሌት፣ ቅድስት፣ መቅደስ አሏት። እሷንም አብነት አድርገው የተሠሩ መቅደሶች አሉ።

• ከመርከቧ በአፍአ ያሉትን ማየ አይኅ ሲያገኛቸው ኖኅን ከእነቤተሰቡ ጥፋቱ አላገኛቸውም፤ እንዲሁም በመልካም አነዋወር በእግዚአብሔር ቤት የሚኖሩ ክርስቲያኖችም መከራ ነፍስ የለባቸውም።

• ከመርከቧ በአፍአ ያሉት ኢ ጥሙቃን በውስጥ ያሉት የጥሙቃን ምሳሌ ነች።

• አንድም መርከብ የእመቤታችን፣ ኖኅ የጌታ፣ ሦስት ክፍል መሆኗ እመቤታችን
የቅድስት ሥላሴ ማደሪያ ለመሆኗ ምሳሌ ነው።

• በአፍአ ያሉት በእመቤታችን ቃል ኪዳን ላመኑ፣ በውስጥ ያሉት በእመቤታችን ቃል ኪዳንያመኑናቸው።

•ከቤተ መቅደስ በአፍአ እመቤታችንን መውደድ አይመችም። ያለ እመቤታችንም ክርስቶስ ያለ ክርስቶስ ክርስትና አይታሰብምና። ከቤተ መቅደስ ከአፍአ ሆነው ነገር እግዚአብሔርን፣ ኪዳነ አበውን፣ ዝክረ ቅዱሳንን ለመናገር አይቻልም። ሰው ለማመን መማር አለበት ለመማርም ወደ መምህራን መቅረብ አለበት የመምህራን መገኛ ደግሞ ቤተ መቅደስ ነው።

፭.፩.፬ የያዕቆብ ሐውልት

ያዕቆብ ከአባቱ ከይስሐቅ ያገኘውን በረከትና ምርቃት ይዞ ከወንድሙ ከኤሳው ፊት ሸሽቶ ወደ አጎቱ ወደ ላባ ቤት ወደ ሶሪያ ሲሄድ ሎዛ ሲደርስ መሸበት። በዚያም በፍኖተ ሎዛ ድንጋይ ተንተርሶ ተኛ፤ሕልምም አለመ። የወርቅ መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ አየ።በመሰላሏም የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡባት ይወርዱባት ነበር። እግዚአብሔርም በመሰላሏ ጫፍ ላይ ቆሞባት ነበር። ድምጽንም አሰምቶ “የአባትህ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ይህችን አንተ የተኛህበትን ምድር ለአንተም ለዚህም እሰጣለሁ የነገርኩህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና።” አለው።

አባታችን ያዕቆብ ከእንቅልፍ ተነስቶ “በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ሥፍራ ነው እኔ አወቅሁም” አለ። ፈራ እንዲህ አለ “ይህ ሥፍራ እንዴት ያስፈራል፤ ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ የሌላ አይደለም፤ይህ የሰማይ ደጅ ነው።” አለ። ተንተርሶበት የነበረውን ድንጋይ ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመው፣ በላዩም ዘይትን አፈሰሰበት ያንንም ሥፍራ ቤቴል /የእግዚአብሔር ቤት/ ብሎ ጠራው። “በምሄድበት ቢጠብቀኝ በጤና ብመለስ እግዚአብሔር አምላክ ይሆንልኛል ለሐውልት የተከልኩት ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል ከሰጠኸኝም ከዐሥር አንዱን እሰጣለሁ።” ሲል ተሳለ ዘፍ ፳፰፥፲-፳፪።

ምሳሌነቱ

• ከሰማይ እስከ ምድር የተተከለችው የወርቅ መሰላል፡- ሰው በአምልኮትና በልጅነት ከእግዚአብሔር ጋር ለሚገናኝባት ቅድስት ቤተ-ክርስቲያን ነው።

• አንድም መሰላል የእመቤታችን ምሳሌ ናት።

• በመሰላሏ ጫፍ ላይ እግዚአብሔር ተገልጦ እንደታየ፡- በእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በተዋሕዶ ሰው በመሆን ተገልጦ ተገልጦባታልና።

• ድንጋዩ የትንቢተ ነቢያት እመቤታችን በነቢያት ትንቢት ጸንታ ለመገኘቷ ነው። አባሕርያቆስ "ነቢያት ትንቢት የተናገሩልሽ ምሳሌ የመሰሉልሽ አንቺ ነሽ" እንዲል።

• መላእክት ሲወጡ ሲወርዱ መታየታቸው ጌታችን ከእመቤታችን ከተወለደ በኋላ
መላእክት ለተልዕኮ የሚወጡ የሚወርዱ ሆነዋልና።

• ከላይ መውረዳቸው ለሰው ልጅ ምሕረትን ከእግዚአብሔር ማምጣቸውን ያመለክታል።

• ከታች ወደ ላይ መውጣታቸው የምዕመናንን ጸሎትና ምጽዋት፣መሥዋዕትና ቁርባን
የማሳረጋቸው ምሳሌ።

• አንድም ከሰማይ መውረዳቸው ጌታ ሰው መሆኑን ሲገልፅ ወደ ላይ መውጣታቸው ጌታ
በ ፴ኛው ቀን ማረጉን ያመለክታል።

•ያዕቆብ የቆሞስ (ጳጳስ)፣ ያቆመው ድንጋይ የቤተክርስቲያን (ታቦት)፤ በድንጋዩ ላይ ያፈሰሰው ዘይት የሜሮን ምሳሌ ነው። ያለ ጳጳሳት ቡራኬ ቤተ ክርስቲያን አይታነጽም ታቦትም አይከብርምና፤ ያለ ቅብዓ ሜሮንም ማክበር አይቻልም።

ቅዱስ ያዕቆብ ከሕልሙ አይቶ ያንን ቦታ "በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ሥፍራ ነው። ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራል፣ ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር

ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፤ ይህም የሰማይ ደጅ ነው።" ብሏል። በዚህች ስፍራ ቤተ መቅደስ ሊያሰኝ የሚችል ሥራ ተሠርቶባታል። አማናዊቱ ቤተ መቅደስ እመቤታችን፣ ቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን ሰዎች ይገኙበታልና ቤቱል የእግዚአብሔር ቤት /የቤተ ክርስቲያን/ ምሳሌ ናት።

፭.፩.፲ ደብረ ታቦር

ደብረ ታቦር የታቦር ተራራ ጌታችን ብርሃነ መለኮቱን የገለጠበት፣ የባሕርይ አምላክነቱን ያስመሰከረበት፣ ምሥጢረ መለኮት የተገለጠበት፣ ቅዱስ ስፍራ ነው። በወንጌል እንደ ተጻፈ ጌታችን ሦስቱን አዕማድ ሐዋርያት አስከትሎ ወደዚህ ተራራ ወጥቷል በዚያም ሙሴ ከመቃብር ኤልያስም ከተሰወረበት ከብሔረ ሕያዋን መጥተው አነጋግረውታል። ክብሩንም ገልጧል። እነርሱም በየበኩላቸው አምላክነቱንና ጌትነቱን መስክረዋል። ይህን በማስመልከት ቅዱስ ማቴዎስ በወንጌሉ ላይ በሰፊው አስፍሮታል ማቴ ፲፯፥፩-፱። ደብረ ታቦር ለአዲስ ኪዳኗ ቤተ መቅደስ ምሳሌ ነው።

, በደብረ ታቦር ጌታችን አምላክነቱን፣ ጌትነቱን፣ ክብሩን እንደ ገለጠ በቤተ መቅደስም ክብሩ ይገለጣል።

, በደብረ ታቦር የብሉይ ኪዳን አባቶች ሙሴና ኤልያስ ከሐዲስ ኪዳንኖቹ አዕማድ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ ያዕቆብና ቅዱስ ዮሐንስ ጋር እንደተገናኙ በአንድነትም እንደቆሙ በቤተ መቅደስም ብሉይ ኪዳን ከሐዲስ ኪዳን ይተርጎማል።

, በደብረ ታቦር የእግዚብሔር ድምፅ እንደተሰማ በቤተ መቅደስ ቃለ እግዚአብሔር ይነገርባታልና

m አዕማድ ሐዋርያት ወደ ደብረ ታቦር እንደ ወጡ እኛም ወደ ቤተ መቅደስ ልንገሰግስ፤ ክብሩን በሚገልጥበት አደባባይ ተገኝተን በቅዱሳት መጻሕፍት ክብሩን ልንመረምር እና ልናደንቅ ልናመሰግን ይገባናል።

የቤት ሥራ

ከታች የተዘረዘሩትን የቤተክርስቲያን ምሳሌዎችን ትርጉም በቡድን ተካፍላችሁ አብራሩ።

-የመምሬ አድባር ዛፍ
-ቀርሜሌዎስ
-የኤልሳዕ ሰገነት
-ቀርሜሌዎስ
-ጌልጌላ
-ደብረ ቅዱስ
-የሞርያም ተራራ

፭.፪ የቤተክርስቲያን ምሳሌዎች በሐዲስ ኪዳን

፭.፪.፩ የአሳ ማጥመጃ መረብ

መረብ በባሕር ውስጥ በተጣለ ጊዜ አሳዎች ሁሉ በመረቡ ውስጥ እንደሚጠመዱ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን በምትሰብከው የወንጌል መረብ ሰውን ከዓለም ለይታ ወደ እቅፏ በማስገባት ከዚህ ዓለም ጥፋት ሁሉ ከዘለዓለም እሳት ትታደጋለች።

- መረቧ - የቤተ-ክርስቲያን
- አጥማጁ - ሰባኪው
- ባሕሩ - የዓለም
- በባሕር ውስጥ ያሉ - የኢ-አማንያን
- በመረቡ ውስጥ የገባ በሰባኪው ቃል አምነው ወደ ቤተ ክርስቲያን አንድነት የተቀላቀሉ ምእመናን ምሳሌ ነው።

፭.፪.፪ የሰርግ ቤት

በሰርግ ቤት ሰባት ነገሮች ይገኛሉ። እነሱም ሙሽሪት ፤ ሙሽራው ፤ ሚዜዎቹ (የሙሽራ እና የሙሽሪት ዘመዶች) የሚበላ እና የሚጠጣ ፤ ደስታ ፤ ምስጋና

አለ። እነዚህ አካላት በሰርግ ቤት የሚገኙ ስለሆነ ጌታችን ቤተ ክርስቲያንን በሰርግ ቤት መስሎ አስተማረ "መንግሥተ ሰማይ ለልጁ ሰርግ የደገሰን ንጉሥን ትመስላለች" ማቴ ፳፪፥፩ እንዲል።

በዚህ ምሳሌ ላይ

- ቤተክርስቲያን በሙሽሪት ትመሰላለች።
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ በሙሽራው።
- መብል መጠጡ የቅዱስ ሥጋ ወደሙ
- ምስጋናው ቤተክርስቲያን የሚከርበው የዉዳሰ ቅዳሰው ምሳሌ ነው።

፩.፪.፫ የአልዓዛር ቤት ምሥጢረ ቁርባን የተደረገባት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ አልዓዛርደቀ መዛሙርቱን ሰብስቦ ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ በገለጠልን መልኩ በጎብስትና በወይኑ ላይ ጸልዮ፣ ባርኮ አመስግኖ አማናዊ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን አቀብሏቸዋል፤ በአጠቃላይ መሥዋዕት ሐዲስን ሠርቶ አስተምሮቸዋል። ቤተ አልዓዛር የቤተ-ክርስቲያን ምሳሌ ነው። ዛሬም ቤተ-ክርስቲያን በጸሎተ ቅዳሴ ጎብስቱ ተለውጦ አማናዊ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑ ተለውጦ አማናዊ ደመ ወልደ እግዚአብሔር ሆኖ በካህኑ አማካኝነት ይፈተትበታልና።

፩.፪.፬ የማርቆስ እናትየማርያም ቤት

አባቶቻችን ቅዱሳንሐዋርያት ከጌታችን ዕርገት በኋላ በማርቆስ እናት ቤት ለጸሎት ይሰበሰቡ ነበር። እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሆነው እግዚአብሔርን በጽናት ደጅ ይጠኑት ነበር። ይህችም ቤተ-ጸሎት የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት። ቅዱሳን ሐዋርያት በማርቆስ እናት ቤት በአንድነት ሆነው ከአምላካቸው ጋር ከተገናኙ በኋላ የተሰጣቸው ተስፋ እንደተፈጸመ ጸጋመንፈስ ቅዱስንም እንደተቀበሉ እኛም ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ተገኝተን በቁርጥ እምነት ደጅ ብንጠና ጸሎታችን ይሰማል።

የመንፈስ ቅዱስም ሀብት ይበዛልናል።

፩.፪.፩ ሕንጸተ ቤተክርስቲያን

‹‹ህንጸተ ቤተ ክርስቲያን›› የቤተ ክርስቲያን መታነጽ ማለት ነው። የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የታነጸችው በሰኔ ፳ቀን ነው። አናጺውም እራሱ ባለቤቱ መድኃኔዓለም ክርስቶስነው፤ ቦታው ፊልጶስዩስ ነው፤ ቤተክርስቲያኗ የተሰየመችው ደግሞ በእመቤታችን ስም ነው።እመቤታችን ካረገች በ፬ኛ ዓመት ጳውሎስና በርናባስ በፊሊጲስዮስ ገብተው አስተምረው ሕዝቡን አሳምነው ካጠመቁ በኋላ ‹‹እንግዲህ ወደ ቤተ ጣዖት አትሂዱ›› አሏቸው። አሕዛብ የነበሩትና አምነው የተጠመቁትም ‹‹የለመድነውን ከከለከላችሁን መካነ ጸሎት ስጡን›› አሏቸው።የከበሩ ሐዋርያትም ወደ ጴጥሮስና ዮሐንስ መልእክት ላኩባቸው። ጴጥሮስና ዮሐንስም ‹‹ያለ ጌታችን ፈቃድ አንዳች ልታደርጉ አይገባምና ጸልዩ እኛም እንጸልያለን›› ብለው መለሱላቸው። ሁሉምሱባኤ ይዘው በጸሎት ተጉ። ጸሎትና ሱባኤያቸውን ከጨረሱ በኋላ ጌታችን በሞት ያረፉትን አስነሥቶ በሕይወት ያሉትንም ደቀመዛሙርቱን በደመና ጠቅሶ ፊልጶስዩስ ሰበሰባቸው።

ጌታችን በኪሩቤል ጀርባ ላይ ሆኖ እልፍ አእላፍ መልአክትን አስከትሎ ወረደ፤ እመቤታችን በቀኙ ነበረች። ቅዱስ ዮሐንስም ‹‹ጌታዬ ለምን ሰበሰብከን?›› ብሎ ጠየቀ።ጌታችንም ‹‹በእናቴ ስም ከጽንፍ እስከ ጽንፍ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነጹ ፈቃዴ ነውና ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ላሳያችሁ ሥርዓት ላስተምራችሁ ነው›› አለው። ይህንን ብሎ ወደ ምሥራቅ ወሰዳቸው። በዚያም ተራርቀው የነበሩ ፫ ደንጊያዎች ነበሩ። ጌታችንም ሦስቱን ድንጋዮችን በተአምራት አቀራርቦ አንሥቶ ጎተታቸው፡ ፡ ድንጋዮቹም እንደ ሰም ተለጠጡ፣ እንደ ግድግዳም ሆኑ። ቁመቱን ወርዱን መጥኖ ለሐዋርያቱ ሰጣቸው። እነርሱም እሳት እንዳየው ሰም ከእጃቸው እየለመለሙ (እየተሳቡ) ቁመቱን ፵፬ ወርዱን ፲፪ ክንድ አድርገው ሠርተውታል። ዳግመኛም የብርሃን ምሰሶ ወረደ በሰማያዊቷ

ኢየሩሳሌም አምሳያ አድርጎ አነጻት ሁለንተናዋም ተጠናቀቀ፡፡ ከዚህም በኋላ ጌታችን ለሐዋርያቱ ‹‹እንግዲህ እናንተም እንዲህ አድርጋችሁ ሥሩ›› ብሏቸው ዐረገ፡፡

ሦስቱ ድንጋዮች የሥላሴን ሦስትነት ወደ አንድ ሆነው አንድ ሕንጻ መታነጹ የሥላሴን አንድነት ያስረዳል፡፡ በአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን መታነጽ ለኛ ለክርስቲያኖች እጅግ ታላቅ በዓልና ደስታነው፡፡ ስለዚች ቤተ ክርስቲያን አባቶች ደማቸውን አፍሰውላታል፣ አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተውላታል፣ አጥንታቸውን ከስክሰውላታል፣ ቆዳቸው ተገፏል፣ በድንጋይ ተወግረዋል፣ በእሳት ተቃጥለዋል፣ በአውሬ ተበልተዋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ግድግዳዋ ውኃ መሠረቷ ደም ነው፡፡ በባሕርይዋ የማትታደስ ነገር ግን ከኃጢአት ከበደል የሚታደሱባት ርትዕት ናት፡፡ ይህች ቤተ ክርስቲያን ‹‹የክርስቶስ አካሉና ሙላቱ ናት፡፡›› ኤፌ ፩፥፲፫፣ ቆላይ ፲፥፲፰፣14፡፡ እናም የዚህችን ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጣስና ትምህርቷን መቆነጻጸል የክርስቶስን አካል ማድማት ነው፡፡ ዳግመኛም በማግሥቱ ሰኔ ፳፭ ቀን ጌታችን ድንግል እናቱን እመቤታችንንና ቅዱሳን መላእክትን አስከትሎ ወረደ፡፡ እመቤታችንን መንበር፣ ጴጥሮስን ተራዳኢ ካህን፣ እስጢፋኖስን ሠራዒ ዲያቆን አድርጎ ቀድሶ ለሐዋርያቱ አቁርቧቸዋልና ፍጹም ደስታም ሆነ፡፡ ዳግመኛም ጴጥሮስን እጁን ጭኖ ፓትርያርክ አድርጎ ሾሞታል፡፡ በዚህም ጊዜ ሰማያውያን መላእክት ምድራውያን ሐዋርያት አንድ ሆነው አመስግነዋል፡፡

ከዚህ በኋላ ሐዋርያት ከጌታችን እንዳዩት በዓለም ዞረው ቤተ ክርስቲያን አንጸዋል፡፡ ከዚያ በፊት የነበረው የእነ ሰሎሞን ቤተ መቅደስ፣ የአይሁድ ምኩራብ፣ የአይሁድ ሥርዓተ አምልኮ መፈጸሚያ እንጂ የአዲስ ኪዳን የቁርባንም ሆነ የጥምቀት ሥርዓት መፈጸሚያ አልነበረም፡፡

እንኪያስ ‹‹ሐዋርያት የት ነበር ሕዝቡን የሚያጠምቁትና የሚያቆርቡት?››

ከተባለ እንደ ማርቆስ እናት ቤታቸው ለሐዋርያት በሰጡ ‹‹በየአማኞቹ ቤት›› ይከናወን ነበር፡፡

የቤት ሥራ

ከታች የተዘረዘሩትን የቤተክርስቲያን የሐዲስ ኪዳን ምሳሌዎችን ትርጉም በቡድን ተካፍላችሁ አብራሩ፡፡

ታላቁ የስንዴ አዝመራ

የከበረ ዕንቁ

መርየት

የሰናፍጭቅንጣት

-ቤተክርስቲያን በተለያየ ጊዜ በተለያየ ምሥጥር ተመስላ እናገኛተለን፡፡ ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ በታንኳ፣ በደብረ ታቦር፣በቀራንዮ፣በገዳመ ቆሮናቶስ፣ ቤተ ሳይዳ በመባል ትጠራለች፡፡

ዋቢ መጻሕፍት

. የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ፤ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ
. ኖኅተ ሰማይ ፤ ዲ/ን ያሬድ ገ/መድኅን
. ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ፤መሠረተ ሕይወት

የሰንበት ት/ቤት አመራር እና መምህራን እንዲሁም ተማሪዎችና ወላጆች በመጽሐፉ ላይ ያላችሁን ማንኛውም አስተያየት እና ግብዓት በሚከተለው አድራሻ ላኩልን


office@eotc-gssu.org
https://t.me/GSSUCurriculum_bot

ሰኔ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰ/ት/ቤቶች አንድነት


የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ስድስተኛ ክፍል









በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
የመንበረ ፓትርያርክ (ዓለም አቀፍ) የሰንበት ት/ቤቶች አንድነት የተዘጋጀ